# የኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ባለሙዎች ማህበር (ኢሚባማ)

## *የ------------------------- ቅ/ማህበር መተዳደሪያ ደንብ*

### *አንቀፅ* 1. *የቅርንጫፍ ማህበሩ መቋቋም*

*የቅርንጫፍ ማህበሩ በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ባለሙያዎች ማህበር መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 3፣ አንቀፅ 17/ ንዑስ አንቀፅ 5 እና የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ለቦረዱ በስጠው ስልጣን መሰረት -------------- ቀን ------------------- ዓ.ም ተቋቁሟል ::*

### *አንቀፅ* 2 . *የቅርንጫፍ ማህበሩ መጠሪያ ስም*

*በኢሚባማ የ------------------------- ቅርንጫፍ ማህበር ተብሎ ይጠራል::*

### *አንቀፅ* 3 . *ዓላማ*

*ቅርንጫፍ ማህበሩ በህብረተሰቡ እና በአካባቢው በሚከናወኑ የሚቲዎሮሎጂ፣ የከባቢ አየር ሳይንስ እና የሀየደሮሎጂ እንቅሰቃሴዎች መካከል ማህበራዊና ሳይንሳዊ ግንኙነት እንዲፈጠር በማድረግ ለሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ እድገት አስተቃጽዖ ደርጋል:: በተጨማሪም በቅርንጫፍ ማህበሩ አባላት መካከል በትብብር የሚሰሩ የምርምር ሥራዎችን ከማበረታት በተጨማሪ በሚቲዎሮሎጂ፣ በከባቢ አየር ሳይንስና በሀይድሮሎጂ ዘርፎች በየግዜው የሚደረስባቸውን አዳዲስ ሳይንሳዊ ግኝቶችን በተመለከተ ተከታታይ ትምህርት የሚገኝባቸውን መንገዶች ያመቻቻል::*

## አንቀፅ 4 . አባልነት

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ባለሙያዎች ማህበር (ኢሚባማ) አባላት የሆኑና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ አካባቢ የሚኖሩ እንዲሁም የህንን መተዳደሪያ ደንብ ተቀብለው የሚያከብሩ ሁሉ የቅርንጫፍ ማህበሩ አባላት መሆን ይችላሉ::

## አንቀፅ 5 . የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ ኃላፊዎች

5.1. ጽ/ቤቱ ሐላፊ እና ገንዘብ ያዥ ይኖረዋል ::

5.2. የሥራ ኃላፊዎቹ በቅርንጫፍ ማህበሩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይመረጣሉ::

## አንቀፅ 6 . ኮሚቴዎች

6.1. የቅርንጫፍ ማህበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ሶስት አባላት ያሉት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቋቁማል:: ይህ ኮሚቴም ሰብሳቢ እና ሁለት አባላት የሚኖሩት ሲሆን የቅርንጫፍ ማህበሩ ጽ/ቤት ሐላፊ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል ::

6.2. የቅርንጫፍ ማህበሩ ፐሬዚዳንት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ሲሆን፤ ቀጥታ ተጠሪነቱ ለኢሚባማ ይሆናል::

6.3. እንደአስፈላጊነቱ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሌሎች ኮሚቴዎችን ማቋቋም ይችላል::

## አንቀፅ 7 . የአባልነት መዋጮ

7.1. የቅርንጫፍ ማህበሩ አባላት የአባልነት መዋጪቸውን የሚያዋጡት ለኢማባማ አባልነታቸው  ብቻ ይሆናል:: ለቅርንጫፍ ማህበሩ ሌላ ተጨማሪ የአባልነት መዋጮ አያደርጉም::

## አንቀፅ 8 . ስብሰባዎች

8.1. ቅርንጫፍ ማህበሩ አንድ ጠቅላላ አመታዊ ስብሰባ ይኖረዋል::

8.2. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው እንደ አስፈላጊነቱ በርካታ ስብሰባዎች ይኖሩታል::

## አንቀፅ 9 . የቅርንጫፍ ማህበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ሥልጣንና ተግባራት

9.1. የቅርንጫፍ ማህበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ሶሰት አባላት ያሉት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቋቋማል ጠንካራ አባላትንም የኮሚቴው አባላት አድርጎ ይመድባል::

9.2. የቅርንጫፍ ማህበሩን የስራና ፋይናንስ እንሆስቃሴ እየመረመረ ለቅርንጫፍ ማህበሩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሪፖርት የሚቀርብ አንድ ኦዲተር ይሰይማል ::

9.3. የስራ መርሃ ግብርንና ባጀትን መርምሮ ያፀድቃል::

9.4. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና የኦፊሰሮችን ስራ እንቅስቃሴ ይገምግማል::

9.5. የቅርንጫፍ ማህበሩ እንቅስቃሴዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ እና እንዲጠናከሩ የማማከርና አመራር የመስጠት ሚና ይጫወታል::

## አንቀፅ 10 . የስራ አመራር ኮሚ□ው ሥልጣንና ተግባራት

10.1. የቅርንጫፍ ማህበሩን የፅ/ቤት ሐላፊ እና ገንዘብ ያዥ ይሰይማል::

10.2. የፅ/ቤት ሐላፊው በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የተወሰኑ ውሳኔውችንና የወጡ እቅዶችን በአግባቡ ማከናወኑን ያረጋግጣል::

10.3. የቅርንጫፍ ማህበሩን የአጭር የመንከለኛና ረጅም ግዜ ዕቅዶችንና ባጀት በማዘጋጀት ለጠቅላላው ስብሰባ አቅርቦ ያፀድቃል::

10.4. ከኦፊሰሮች ጋር በመተባበር የቅርጫፍ ማህበሩን ጠቅላላ ስብሰባ እነዲዘጋጅ እና እንዲከናወን ያደርጋል::

10.5. የቅርንጫፍ ማህበሩ ስራ ክንውንና የፋይናንስ ሪፖርት በአመት ሁለት ግዜ መቅረቡን ያረጋግጣል::

10.6. እንደአስፈላጊነቱ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል::

## አንቀፅ 11 . የቅርንጫፍ ማህበሩ ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባራት

11.1. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ስብሰባ እና የጠቅላላ ስብሰባን ይመራል::

11.2. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ውሳኔዎች ለጠቅላላው ስብሰባ ያቀርባል::

11.3 የቅርንጫፍ ማህበሩ ስራዎች እና ፋይናንስ ስራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ይከታተላል::

11.4. የቅርንጫፍ ማህበሩ ስራ ክንውንና የፋይናንስ ሪፖርት በአመት ሁለት ግዜ ለኢሚባማ ዋና ፅ/ቤት መቅረቡን ያረጋግጣል::

11.5. የቅርጫፍ ማህበሩ አመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ በታቀደለት ግዜ መከናወኑን እና ለኢሚባማ ዋናው ፅ/ቤት ተገቢው ሪፖርት መቅረቡን ያረጋግጣል::

## አንቀፅ 12 . የቅርንጫፍ ፅ/ቤት ሐላፊው ሥልጣንና ተግባራት

12.1. የቅርንጫፍ ማህበሩን የገንዘብ እንቅስቃሴ በተመለከተ የወጪዎችን ህጋዊነት በማረጋገጥ ከገንዘብ ያዡ ጋር በጋራ ቼኮች ላይ ፈርማል::

12.2. የቅርንጫፍ ማህበሩን ጠቅላላ ስብሰባ ውሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል::

12.3. የቅርንጫፍ ማህበሩን ሩብ አመት እና አመታዊ የስራ ክንውንና የፋይናንስ ሪፖርት በማዘጋጀት ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያቀርባል፤ ይህም ሪፖርት ለኢሚባማ ዋና ፅ/ቤት መድረሱን ያረጋግጣል።

12.4. የቅርንጫፍ ማህበሩን መርሃግብር፣ ባጀት እና የድረጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ በማቅረብ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያፀድቃል።

12.5. የቅርንጫፍ ማህበሩን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ይመራል።

12.6. የቅርንጫፍ ማህበሩን ሌሎች የስራ አመራር ውሳኔዎችን ይወስናል።

12.7. የቅርጫፍ ማህበሩን አመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ ሪፖርት ለኢሚባማ ዋና ፅ/ቤት ያቀርባል።

12.8. ሌሎች ተያያዥ ስራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ያረጋግጣል።

## አንቀፅ 13 . የቅርንጫፍ ፅ/ቤት ገንዘብ ያዥ ሥልጣንና ተግባራት

13.1. የቅርንጫፍ ማህበሩ አባላት መዋጪቸውን በወቅቱ መክፈላቸውንና ይህም በአግባቡ መዘገቡን ያረጋግጣል።

13.2. የቅርንጫፍ ማህበሩ ገቢና ወጪ ሰነዶች ላይ ይፈርማል፤ እንዲሁም ገቢና ወጪ ሥርዐቶችን ይቆጣጠራል፣ አጠቃላይ የሂሳብ ስራዎችን ያከናውናል።

13.3. የሂሳብ መዛግብት በቅርንጫፍ ማህበሩ ኦዲተር መመርመራቸውን ያረጋግጣል።

13.4. የቅርንጫፍ ማህበሩን ሂሳብ ወጪ አዘጋጅቶ በፅ/ቤት ሐላፊው አፀድቆ ከፅ/ቤት ሐላፊው ጋር በጋራ በሚፈረም ቼክ ህጋዊ የገንዘብ ዝውውርና  የገንዘብ ወጪ ስራዎችን ያከናውናል።

13.5. የቅርንጫፍ ማህበሩ ሂሳብ መዛግብት እና ሌሎች ተጓዳኝ ሰነዶችን በአግባቡ ይይዛል።

## አንቀፅ 14. የአባላት መዋጮ አሰባሰብና የገንዘብ ምንጭ

14.1. የቅርንጫፍ ማህበሩ የአባላት መዋጮን ከአባላቱ በሙሉ ሰብሰቦ ወደ ኢሚባማ የባንክ ሂሳብ እንዲላክ ያደርጋል፡፡

14.2. የኢሚባማ ቦርድ ለቅርንጫፍ ማህበሩ የስራ ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት ይመድባል ፡፡

## አንቀፅ 15. የቅርንጫፍ ማህበሩ መፍረስ

15.1. የቅርንጫፍ ማህበሩ ሊፈርስ የሚችለው ለኢሚባማ ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ እንዲፈርስ ሲወሰን ብቻ ነው፡፡

## አንቀፅ 16. የደንብ ማሻሻያ

16.1. አስፈላጊ ሲሆን የቅርንጫፍ ማህበሩ ደንብ ለኢሚባማ ቦርድ ቀርቦ እንዲሻሻል ሲፈቀድ ሊሻሻል ይችላል፡፡